የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ሕዳር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.4
ADDIS ABABA 24th November, 2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፮/፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዛምቢያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በኢኮኖሚ፣ በሳይንስና ቴክኒክ ዘርፍ ለመተባበር የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …ገጽ ፱ሺ፱፻፶፰

## Content

Proclamation No. 1056/2017

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Zambia on Economic, Scientific and Technical Cooperation ratification Proclamation ………..…….. --Page 9958

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፮/፪ሺ፲

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዛምቢያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በኢኮኖሚ፣ በሳይንስና ቴክኒክ ዘርፍ ለመተባበር የተደረገውን ስምምነት ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዛምቢያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በኢኮኖሚ፣ በሳይንስና ቴክኒክ ዘርፍ ለመተባበር ስምምነት ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም. በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዛምቢያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በኢኮኖሚ፣ በሳይንስና ቴክኒክ ዘርፍ ለመተባበር የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፮/፪ሺ፲” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1056/2017

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF ZAMBIA ON ECONOMIC, SCIENTIFIC AND TECHNICAL COOPRATION</u>**

WHEREAS, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Zambia have signed an Agreement on Economic, Scientific and Technical Cooperation, in Addis Ababa, on the 14th day of July, 2012;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 2nd day of November, 2017;

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Zambia on Economic, Scientific and Technical Cooperation

**፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ**

፩/ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዛምቢያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም. በአዲስ አበባ የተፈረመው የኢኮኖሚ፣ የሳይንስና ቴክኒክ ትብብር ስምምነት ፀድቋል፡፡

፪/ በዚህ ስምምነት አንቀፅ 9 ላይ የሚደረግ መሠረታዊ ማሻሻያ በስምምነቱ አንቀፅ 11(1) መሠረት ወደ ሥራ ይገባል

**፫. አስፈፃሚ አካል**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን ስምምነት ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሕዳር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም.**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

ratification Proclamation No.1056/2017”.

**2. Ratification of the Agreement**

1/ The Agreement on Economic, Scientific and Technical Cooperation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Zambia, which is signed in Addis Ababa on the 14th day of July, 2012, is hereby ratified.

2/ Any Substantive amendment made in this agreement according to article 9 shall enter in to force in accordance with article 11(1)of this agreement

**3. Implementing Organs**

The Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa on this 24th day of November, 2017.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**